*ሰኔ 2002 ዓ/ም*

# *የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

## *በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ*

## *አጭር ማብራሪያ*

**አዲስ አበባ**

**ሰኔ 2002 ዓ/ም**

# በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ

## 1 ጠቀሜታው

በኢትዮጵያ በገቢ አሰባሰብ ዘርፍ እየተካሄዱ ካሉት የአሰራር ስርአት ማሻሻያዎች አንዱ የሆነው ዘመናዊ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ስርአት /Biometric Tax Payers Identification Number/ ዝርጋታ ፕሮጀክት ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብ፣ ለማጠናቀርና ለማሠራጨት እንዲሁም ለግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረተ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ነው ፡፡

## 2.ዋና ዓላማው

- ግብር/ታክስ መክፈል የሚገባውን ግለሰብ ወይም ድርጅት የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ፣ አድራሻ፣ የቀን ወይም የዓመት ጠቅላላ ገቢና የሚከፈለው የግብርና ታክስ አይነት ለይቶ ለማወቅ፣
- ግብር/ታክስ በወቅቱ አስታውቀው የሚከፍሉና የማይከፍሉ ግብር ከፋዮችን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራርን ለመዘርጋት፣
- ከሦስተኛ ወገን የሚገኝ የግብር ከፋዩን መረጃ በተጠናከረ ሁኔታ በአግባቡ ሰብስቦ ለመያዝ እና ግብር ከፋዩ ከሚያቀርበው መረጃ ጋር በቀላሉ ለማመሳከር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ነው፣
- ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በትክክለኛ መረጃ የተመሰረተ ቀልጣፋ የግብርና/ቀረጥ አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው፡፡

## 3. ምዝገባው የሚያካትተው ፡-

- በማንኛውም ገቢ ማስገኛ ንግድ ዘርፍ የተሰማራ ግለሰብን፣
- ማንኛውም ግብር ከፋይ የሆነ የመንግስት፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት እና የግል ድርጅት ተቀጣሪዎች፣
- በወጪ መጋራት ስረአት ተሳታፊ የሆኑ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ነው፡፡

Φ ምዝገባው ከሚመለከታቸው ተሳታፊዎች ውስጥ በተለይ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያ ሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ በስማቸው የሚያንቀሳቅሱት ማንኛውም ገቢ የሚያስገኝ ኢንቨስትመንት ወይም ንግድ ዘርፍ /ቤት ማከራየትን ጨምሮ/ ፣ ኑሯቸው ከኢትዮጵያ ውጪ ሆኖ ስራውን በተወካይ በማንቀሳቀስ ገቢ የሚያገኙ ፣ግብር እየከፈሉ ያሉ ወይም መክፈል ያለባቸው ግለሰቦችን ያካትታል፡፡

Φ ሆኖም የኩባንያ ባለ አክሲዮን ግለሰቦችን (Share holders) ፣በህጋዊ ሰውነት የተቋቋሙ የግል ድርጅቶች / Private Limited Company, Share Company, Partnership / ተቋሞችን ምዝገባው ለጊዜው አይመለከታቸውም፡፡

## 4. አስፈላጊ መረጃዎች

- ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /ፓስፖርት፤
- ቀደም ሲል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /ባለ አስር አሃዝ / ካለ ማቅረብ፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌለ የንግድ ፈቃድ / ምዝገባ ማቅረብ፤
- የውጭ ሃገር ዜጋ ሆነው ትውልደ ኢትዮጵያ ከሆኑ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ፤
- የግራና የቀኝ አመልካች ጣቶችን አሻራ እና ፎቶ መስጠት፤
- የምዝገባ ደረሰኝ መቀበል፤

## 5. የአለመመዝገብ ጉዳት

- ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ከግብር/ቀረጥ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት በጣት አሻራ የተደገፈ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፤
- የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ የሚሰጥ ወይም የሚያድስ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላላቀረበ ሰው ፈቃድ አይሰጥም ወይም አያድስም፡፡ በተጨማሪም በግብር ህግ የተመለከቱት ሌሎች አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*አዲስ አበባ*